# 7ኛ ትምህርት

ጥቅምት 26-ህዳር 2 2009 ዓ.ም Nov 5-11

## የበቀል ቅጣት

ሰንበት ከሰዓት

**ለዚህ ሳምንት ጥናት የሚከተሉትን ጥቅሶች አንብቡ፡- ኢዮብ 8¸1-22፣ ኢዮብ 11¸1-20፣ ኢሣ. 40¸12-14፣ ዘፍ. 6¸5-8፣ 2ኛ ጴጥ. 3¸5-7**

**መታሰቢያ ጥቅስ፡-**

"የእግዚአብሔርን ጥልቅ ነገር ልትመረምር ትችላለህን? ወይስ ሁሉን የሚችል አምላክ ፈጽመህ ልትመረምር ትችላለህን?" ኢዮብ 11:7

የ ሰው ልጆች መከራ ተስፋ አስቆራጭ በሆነ ሁኔታ ሰብዓዊውን ዘር እንዳስጨነቀ ቀጥሏል፡፡ መልካም የምንላቸው ሰዎች ከባድ ሀዘን ውስጥ ሲገቡ ክፉዎች ደግሞ ያለምንም ቅጣት ሲተው እንመለከታለን፡፡ ከጥቂት አመታት በፊት "መልካም ሰዎች ክፉ ነገር ለምን ይደርስባቸዋል?" በሚል ርዕስ አንድ መፅሀፍ ታትሞ ነበር፡፡ ባለፈው ሺህ ዓመት ይህንን ጥያቄ በአጥጋቢ ሁኔታ ለለመመለስ ከሞከሩ ከቁጥር በላይ የሆኑ ሙከራዎች ሌሎች ፀሀፍት እና ሊቃውንትም በዚህ ችግር ዙሪያ ምላሽ ለመስጠት ያደረጉትን ጥረት በፅሁፍ አስፍረዋል፡፡ ትክክለኛውን ምላሽ ግን ያገኙት አይመስሉም፡፡

ቀጥለን የምናጠናው የኢዮብ መፅሀፍ የቀረበበትን አውድ ነው፡፡ በዚያም እንደ ኢዮብ ያሉ መልካም ሰዎች ለምን በዚህ ምድር እንደሚሰቃዩ ማጥናት እንቀጥላለን፡፡

የኢዮብ መፅሀፍ እንደሌሎች መፅሀፍት በችግሩ ዙሪያ የተሰነዘሩ ሰብዓዊ አመለካከቶችን አዝሏል፡፡ ልዩነቱ ግን መፅሀፉ ቅዱስ መፅሀፍ እንደመሆኑ በዋነኝነት እግዚአብሔር በጉዳዩ ዙሪያ ያለውን አመለካከት ማንፀባረቁ ነው፡፡ በዚህ ሳምንት ጥናታችን ኢዮብን በስቃዩ ወቅት ሊጎበኙት ከመጡት ሰዎች አንደበት የተነገሩ ቃላትን እንመለከታለን፡፡

**ፀሀፍቱ እና ሊቃውንቱ እንዳሳቱት እነዚህም ሰዎች የሰው ልጅን ስቃይ መንስኤ ለመረዳት ካደረጉት የከሸፈ ጥረት ምን እንማራለን?**

**የዚህ ሳምንት ትምህርት አጥንተው ለህዳር 3 ሰንበት ይዘጋጁ፡፡**

*እሁድ ጥቅምት 27* *Nov 6*

## ተደራራቢ ክሶች

ኤልፋዝ የሰነዘራቸው የምክር ቃላት ያን ያህል የከፋ ባይሆንም ቀጥሎ ግን ኢዮብ ከበልዳዶስ የተሰነዘሩትን ቃላት ማስተናገድ ጀመረ፡፡ በልዳዶስ ከኤልፋዝ ጋር ተመሳሳይነት ያለው ሃሣብ በማንሳት ነበር ምክሩን የጀመረው፤ እሱ ግን እንደአለመታደል ከኤልፋዝም ይልቅ ጠንካራ እና አስከፊ ቃላትን ነበር የተናገረው፡፡ ልጆቹን በሞት ወደተነጠቀ ሰው ዘንድ ሄዳችሁ "ልጆችህ እግዚአብሐርን በድለውት እንደሆነ፤ እርሱ በበደላቸው እጅ ጥሏቸዋል፡፡" (ኢዮብ 8¸4) ስትሉት አስቡ እስቲ፡፡

በእውነቱ ይህ እንቆቅልሽ ነው! ምክንያቱም የኢዮብ መፅሀፍ የመጀመሪያዎቹ ምዕራፎች ምን አልባት ለጥፋት የሚያደርስ ሀጥያት ሰርተው እንደሆነ በማለት ኢዮብ ስለልጆቹ መስዋዕት እንዳቀረበ በግልፅ ይነግሩናል፡፡ (ኢዮብ 1፡5) በዚህ ክፍል አንድ ተቃርኖ እንመለከታለን፡፡ ያም በኢዮብ ድርጊት የተገለፀውን የፀጋ ማስተዋል እና በበልዳዶስ ቃላት ውስጥ የተገለፀው አክራሪ እና በቀለኛ የህግ አቀንቃኝነት መሀል ያለን ተቃርኖ ነው፡፡ ጉዳዩን ከዚህ በላይ አስከፊ የሚያደርገው ደግሞ በልዳዶስ እነዛን ቃላት የሚናገረው እግዚአብሔርን ለመከላከል እና ከተጠያቂነት ለማዳን መሆኑ ነው፡፡

**ኢዮብ 8¸1-22 ያንብቡ። የበልዳዶስ ሃሣብ ምንድነው? የሚናገረው ምን ያህል እውነትነት አለው? ማለትም የበልዳዶስን ቃላት ለኢዮብ እንደተናገሩ ሳይሆን እንደ አንድ ሃሣብ ብንቃኛቸው ስህተት ይኖራቸዋል? ከጠቀሳቸው ሃሣቦች የትኞቹ ናቸው የተሳሳቱት?**

በልዳዶስ እዚህ ጋ የተናገራቸው ቃላትስ ምን ስህተት አላቸው? (ኢዮብ 8¸4)ይህ እውነትም ሀይለኛና ትክክለኛ የሆነ መፅሀፍ ቅዱሳዊ ሃሣብ ነው። (ያዕ. 4¸14) በተያያዥ እግዚአብሔርን የሚረሳ እና ተስፋውን በምድራዊ ነገር የሚያደርግ ሰው እምነቱ ከሸረሪት ድር የማይጠነክር እንደሆነ በልዳዶስ ያቀረበው ሃሣብ ምን ስህተት ሊወጣለት ይችላል? ይህ ሙሉ በሙሉ መፅሀፍ ቅዱሳዊ ሃሣብ ነው።

ምን አልባትም ችግሩ በልዳዶስ የእግዚአብሔርን አንዱን ገፅታ ብቻ እያቀረበ መሆኑ ነው። ይህ ማለት በአንድ መንገድ መሀል መራመድ ሲገባን ከመንገዱ በስተቀኝ ወይም በስተግራ በሚገኝ የውሃ ፍሳሽ ቦይ ውስጥ እንደመራመድ ነው። ለምሳሌ አንድ ሰው በህግ፣ በፍትህ እና በመታዘዝ ላይ ሲያተኩርና ሌላው በፀጋ፣ በምህረት እና በምልጃ ላይ ሊያተኩር ይችላል። ከእነዚህ በአንዱ ላይ ብቻ ሙሉ በሙሉ ማተኮር ወደ ተዛባ የእግዚአብሔር ምስል እና ስህተት ሊመራን ይችላል። በዚህም ቦታ የምንመለከተው ተመሳሳይ ችግር ነው።

**እንደ አንድ ሰብዓዊ ዘር ከሌሎች ጋር በምናደርገው ውይይትም ሆነ በአስተምሮአችን በፀጋ እና በህግ መሀል ትክክለኛ የሆነ ሚዛን ሊኖረን ይገባል። ሆኖም ግን ሰው በመሆናችን ከሁለት ወደ አንዱ እናጋድላለን። እንደው ብንሳሳት እንኳን ሌሎችን ለመምከር በየትኛው መልክ ብንሳሳት ይሻላል? ለምን?**

*ሰኞ ጥቅምት 28* *Nov 7*

## "ለጥፋትህ ከሚገባህ በታች"

"የእግዚአብሔርን ጥልቅ ነገር ልትመረምር ትችላለህን? ወይስ ሁሉን የሚችል አምላክ ፈጽመህ ልትመረምር ትችላለህን? ከሰማይ ይልቅ ከፍ ይላል ምን ልታደር ግትችላለህ? ከሲኦልም ይልቅ ይጠልቃል፤ ምን ልታውቅ ትችላለህ? ርዝመቱ ከምድር ይልቅ ይረዝማል፣ ከባሕርም ይልቅይሰፋል።" (ኢዮብ 11¸7-9)፤ በተጨማሪም ኢሳ. 40¸12-14)

**እነዚህ ጥቅሶች ምን አይነት መልዕክት ይዘዋል? ይህንን መልዕክት ሁልግዜ ማስተዋል የሚያስፈልገን ለምንድነው?**

በጥቅሱ ውስጥ የቀረቡት ውብ ገለጻዎች ስለእግዚአብሔር የማናውቀው በጣም ብዙ ነገር እንዳለ እና እርሱን ለመመርመር በራሳችን የምናደርጋቸው ጥረቶች ሁሉ በጣም ጥቂት መረጃ ብቻ እንደሚያስገኙልን ያስረዳሉ። ሪቻርድ ሮርቲ፤ በ20ኛው ክፍለ ዘመን ተነስተው ከነበሩ ፈላስፎች መሀል አንዱ ሲሆን በዘመኑ በዋነኝነት ያንፀባረቀው ሃሣብም እውነታን (Reality) መረዳት የማንችል በመሆኑ ጥረታችንን ማቋረጥ እንዳለብን የሚያትት ነበር። ቀጥሎም እውነታን ለመረዳት ከመሞከር ይልቅ እኛ ማድረግ የሚኖርብን ከእውነታው ጋር ተስማምቶ መኖር እንደሆነም ሮርቲ አክሏል።

የ2000 ዓመታት የምዕራቡ ዓለም ፍልስፍና በእንደዚህ አይነት የሽንፈት ቃላት መጠናቀቁ የሚገርም ነው፡ ፡ስለምንኖርበት የገሀዱ ዓለም እውነታ ለመረዳት የምናደርገው ጥረት (ፍለጋ) ሁሉ ያለምንም ውጤት የሚጠናቀቅ ከሆነ ታድያ ይህንን አለም ወደ ህያውነት የጠራውን ፈጣሪ በጥረት እና በፍለጋ ማን ሊረዳው ይችላል? እርሱማ ከዚህ ዓለም ሁሉ እጅግ የላቀ ነው። ሮትሪ በይፋ ያሳሰበው አንድ ነገር ቢኖር ዝም ብሎ ከመፅሐፍቅዱስ ማንበቡ የተሻለ እንደሆነ ነው።

እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት የጥበብ ቃላት ሶስተኛው የኢዮብ መካሪ ሶፋር ለኢዮብ ከሰነዘረው የተሳሳተ ትንተና ጋር ተያይዘው የቀረቡ ናቸው።

**ኢዮብ 11፣1-20 ያንብቡ። ሶፋር ከተናገረው ነገር መሀል ትክክል የሆነው የቱ ነው? ጠቅለል አድርገን ስንመለከተው የተሳሳተ የሚሆነው ለምን ነው? (እንዴት ነው)**

እንደ ኢዮብ ባለ ሁኔታ እየተሰቃየ ወዳለ ሰው ጠጋ በማለት "ዋጋህን ነው ያገኘሽው! እንደውም ከሚገባህ በታች ነው ያገኘሽው!" ማለት እጅግ የሚከብድ ነው። ከዚህ ሁሉ በላይ የከፋው ነገር ደግሞ ሶፋር እና ሌሎችም መካሪዎች እንዳዚህ የሚሉት እግዚአብሔር በሥራው ትክክል መሆኑን ለማስረዳት መሆኑ ነው፡ ፡

**አንዳንድ ግዜ ስለእግዚአብሔር ባህሪ የምናገኘውን እውነታ ሁሉ ወዲያውኑ ማንፀባረቅ አያስፈልግም። የእግዚአብሔርን ባህሪ ገልጦ ለማውራት የሚያስፈልጉን ተጨማሪ ነገሮች ምንድናቸው?**

## መለኮታዊ ቅጣት

የኢዮብ ሶስቱ ወዳጆች ስለእግዚአብሔር የተወሰነ መረዳት እንደነበራቸው ግልፅ ነው፡፡ ለእግዚአብሔር ጥብቅና ለመቆም ያሰቡትም ከበጎ ሃሣብ በመነሳሳት ነበር፡፡ እንደተመለከትነው በእንደ ኢዮብ አይነት ሁኔታ ለነበረ ሰው የሰነዘሯቸው ቃላት መረን የለቀቁ ቢሆኑም ወሳኝ የሆነ መልዕክት እያስተላለፉ ነበር፡፡ የመልዕክታቸው ጭብጥም እግዚአብሔር ፃድቅ ፈራጅ (ፍትሃዊ) እንደሆነ፤ ሐጥያት መለኮታዊ የበቀል ቅጣት የሚያስከትል እንደሆነ እና መልካምነት ደግሞ የተለየ በረከት እንደሚያወርድ ነው፡፡

እነዚህ ሰዎች የነበሩበትን ዘመን በትክክል ማስቀመጥ ባይቻልም፤ ሙሴ የኢዮብን መፅሃፍን በሞሪያም በረሀ ሆኖ እንደፃፈ ስለሚታመን፤ እስራኤልን ከግብፅ ከማውጣቱ በፊት ባሉት ግዜያት እንደኖሩ ይታመናል፡፡ ከጥፋት ውሃ በኂላ እንደኖሩ መገመትም ይቻላል፡፡

**ዘፍ. 6¸5-8 ይመልከቱ፡፡ ኤልፋዝ፣ በልዳዶስ እና ሶፋር ስለጥፋት ውሃ የነበራቸው እውቀት ምን ያህል አመለካከታቸው ላይ ተፅዕኖ አሳድሯል?**

በእርግጥም የጥፋት ውሃ ታሪክ እግዚአብሔር በሀጥያት ላይ የሚያመጣውን መለኮታዊ ቅጣት የሚያሳይ ነው፡፡ በታሪኩ ውስጥ በተለየ ሁኔታ ቅጣት ሚገባቸው ሆኖ የተገኙ ሰዎች ላይ እግዚአብሔር የሚያመጣውን ጥፋት እንመለከታለን፡፡ ነገር ግን እዛ ውስጥም በዘፍጥረት 6፡8 ላይ እንደምንመለከተው ፀጋ ተገልጧል፡፡ ኤለን ዋይት እንዲህ በማለት ፅፋለች፤ "በመርከቢቷ ላይ ያረፈው እያንዳንዱ የመዶሻ ምት ለህዝቡ የቀረበ ስብከት ነበር"፡፡ የትንቢት መንፈስ ፅሁፎች፤የሆነ ሆኖ በኢዮብ መፅሀፍ ውስጥ የኢዮብ መካሪዎች ያስተላለፉትን መልዕክትም በተወሰነ መልኩ እንመለከታለን፡፡

**ተመሳሳይ የሆነ የበቀል ቅጣት በእነዚህ ጥቅሶች ውስጥ እንዴት ተገልፆ ይገኛል? ዘፍ 13¸13፤ 18.20-32፤ 19¸24-25?**

ኤልፋዝ፣ በልዳዶስ እና ሶፋር ስለእነዚህ ክስተቶች ቢያውቁምባያውቁ፤ ክስተቶቹ ግን እግዚአብሔር በሀጥያት ላይ በቀጥታ የሚያወርደውን ጥፋት ይገልፃሉ። እግዚአብሔር ሀጥያተኞችን ከነሐጥያታቸው በመተው ሀጥያታቸው እነርሱን እንዲያጠፋቸው የሚተው አምላክ አይደለም። በጥፋት ውሃ እንዳየነው ፍርዱም፤ በቀጥታ የሚተላለፈው ከእግዚአብሔር ዙፋን ነው። በታሪኩ ላይ እግዚአብሔር በሀጥያት ላይ የሚፈርድ እና የሚያጠፋም ሆኖ እናገኘዋለን።

**በይበልጥ በእግዚአብሔር ፍቅር፤ ፀጋና ምህረት ማተኮር እንዳለብን ሁሉ ፅድቁን (ቅን ፈራጅነቱንም) መርሳት የሌለብን ለምንድ ነው? እስከ ዛሬ ድረስ ቅጣታቸውን ሳይቀበሉ ስለቀሩ ክፉ ሰዎች ያስቡ። ይህ በምንም አይነት ሁኔታ እና ግዜ ሊመጣ ስለሚችለው መለኮታዊ ቅጣት አስፈላጊነት ምን ይነግረናል?**

*ረቡዕ ጥቅምት 30* *Nov 8*

## "እግዚአብሔር አዲስ ነገር ቢፈጥር"

የኢዮብ መፅሀፍ ገፀ ባህርያት ካለፉ በኋላም በመፅሀፍ ቅዱስ ውስጥ እግዚአብሔር በክፉዎች ላይ ያወረደውን ቀጥተኛ መለኮታዊ ቅጣት እንዲሁም ለታማኞች የሰጠውን በረከት ተመዝግቦ እናገኛለን።

ይህ ጥቅስ ለታዛዦች ከተሰጠው ተስፋ ምን ይነግረናል? (ዘዳ. 6:24፣25) ብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር እርሱን ለታዘዙ ህዝቦች ሊሰጥ በተደጋጋሚ ቃል በገባላቸው በረከቶች እና የደላደለ ህይወት ተስፋ ቃላት የተሞላ ነው። በመሆኑም የኢዮብ መካሪዎች ለእግዚአብሔር እና ለህግጋቶቹ በመታዘዝ የቀና ህይወት ለመኖር ለቆረጡ ሰዎች የሚሰጠውን በረከት በተመለከተ የተናገሩትን እናነባለን።

በእርግጥ ብሉይ ኪዳን በተመሳሳይ አመፅ ላይ የሚወርደውን መለኮታዊ ቅጣትንም አስመልክቶ በተደጋጋሚ በቀረቡ ማስጠንቀቂያዎች የተሞላ ነው። እግዚአብሔር በሲና ተራራ ከእስራኤል ጋር ከገባው ቃልኪዳን በኋላ ያለው አብዛኛው የብሉይ ኪዳን ክፍል እስራኤል በአለመታዘዛቸው ምክንያት ሊመጣባቸው ስላለው ቅጣት እያስጠነቀቀ የሚተርክ ነው።

"ነገር ግን የእግዚአብሔርን ቃል ባትሰሙ፥ በእግዚአብሔርም ትእዛዝ ላይ ብታምፁ፣ በእናንተና በንጉሣችሁ ላይ የእግዚአብሔር እጅ ትሆናለች።" 1ኛ ሳሙ. 12:15

**ዘሁ.16፣1-33 ያንብቡ፡፡ ይህ ክስተት ስለመለኮታዊ የበቀል ቅጣት ምን ያስተምረናል?**

የእነዚህን አመፀኛ ሰዎች ጥፋት "ሀጥያት እራሱ ሀጥያተኞችን ላይ ጥፋት ያስከትላል፡፡" ለሚለው አባባል እንደማሳያ ማቅረብ አንችልም፡፡ እነዚህ ሰዎች ለሀጥያት እና አመፃቸው መለኮታዊ የበቀል ቅጣት የተቀበሉት በቀጥታ ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው፡፡ እዚህ ቦታ ላይ መለኮታዊ የእግዚአብሔር ሀይል መገለጥ እንመለከታለን፤ የተፈጥሮ ህጎች ሳይቀሩ የተለወጡ ይመስላል፡፡

እዚህ ቦታ ላይ የምንመለከተው ቢፈጥር የሚለው ቃል ዘፍ. 1፡1 ላይ ካለው "ፈጠረ" ከሚለው ቃል ጋር ተመሳሳይ ስርወ ቃል አለው፡፡ እግዚአብሔር በአመፀኞቹ ላይ ፈጣን ጥፋት በቀጥታ የላከባቸው እርሱ ራሱ መሆኑን ሁሉም እንዲያውቁ ፈልጎ ነው፡፡

*ሐሙስ ህዳር 1* *Nov 9*

## "ሁለተኛው ሞት"

ከሁሉ በላይ ታላቁና ሀይለኛው የበቀል ፍርድ በመፅሐፍ ቅዱስ ሁለተኛ ሞት (ራዕይ 20፡14) ተብሎ በተጠቀሰው ጥፋት በዘመን መጨረሻ የሚፈፀመው እንደሆነ ጥርጥር የለውም፡፡ ይህ ሞት ግን ለሁሉም የአዳም ዘር አይቀሬ የሆነው ሞት እንዳልሆነ ልብ ይሏል፡፡ በዘመን መጨረሻ ሁለተኛው አዳም እየሱስ ክርስቶስ ፃድቃንን ከዚህ ሁለተኛ ሞት ከተባለው ጥፋት ያስጥላቸውል (1ኛ ቆሮ. 15፡26) በተፃራሪው ደግሞ ይህ ሁለተኛ ሞት በመባል የተጠቀሰው ቅጣት ፤ በብሉይ ኪዳን ዘመን እንደደረሱት ጥፋቶች፤ ንስሀ በመግባት በኢየሱስ ክርስቶስ ድነት ላላገኙሀጢአን የሚመጣ የእግዚአብሔር ቀጥተኛ ቅጣትም ነው፡፡

**2ኛ ጴጥ.3፣5-7 ያንብቡ፡፡ በእየሱስስላላመኑ ሰዎች ዕጣ ፈንታ መፅሀፍ ቅዱስ ምን እያለን ነው ያለው?**

"እነሆ፣ እንደ ምድጃ እሳት የሚነድድ ቀን ይመጣል ትዕቢተኞችና ኃጢአትን የሚሠሩ ሁሉ ገለባ ይሆናሉ የሚመጣውም ቀን ያቃጥላቸዋል፡፡ የሰማይም ፍጥረት በትልቅ ትኵሳት ይቀልጣል፥ ምድርም በእርስዋም

ላይ የተደረገው ሁሉ ይቃጠላል፡፡" ሚል. 4፡1፣2፤2ኛ ጴጥ. 3¸10

የምድር ገፅ አንድ ትልቅ የቀለጠ አካል፤ የሚንቦገቦግ የእሳት ባህር ይመስላል፡፡ ሐጥአንም የመጨረሻ ቅጣታቸውን የሚቀበሉበት የፍርድ ሰዓት ይሆናል፡፡ (ኢሣ. 34፡8፤ ኤለን ጂ. ኋይት፣ ታላቁ ተጋድሎ ገፅ 672 . . .) የኢዮብ መካሪዎች እንዳብራሩት ሐጥያት በሐጥያተኛው ላይ የሚያደርሰው ጥፋት ቢኖርም ነገር ግን እግዚአብሔር እራሱ በሀጥያተኛው ላይ በቀጥታ ቅጣት የሚያመጣበትም ግዜ ይኖራል፡፡ የዚህ ምድር ሰቆቃ ሁሉ ምክንያት ሀጥያት እንደሆነ ግልፅ ነው፡፡ ነገር ግን ሰቆቃና ችግር ሁሉ በሀጥያተኛው ላይ ከእግዚአብሔር የሚወርድ ቅጣት ነው ማለትም አይቻልም ኢዮብ ላይ የደረሰውም በሌሎችም በርካታ ሰዎች ላይ የምናየውም ሰቆቃ የሀጥያተኛው ቅጣት አይደለም፡፡

እውነታው እኛ የታላቁ ተጋድሎ አካል መሆናችን እና ክፋት ሊያደርስብን የሚወድ ጠላት መኖሩ ነው፡፡ አስደሳቹ ዜና ግን በዚህ ሁሉ መሀል እግዚአብሔር ለእኛ የሚቆምልን መሆኑ ነው፡፡ አሁን ላይ የሚገጥሙን ፈተናዎች ምንም ይሁኑ ምን፣ የእነዚህ መከራዎች ጦስ ምንም ይሁን ምን የተረጋገጠ የእግዚአብሔር ተስፋ አለን፡፡ ይህ ፍቅር ደግሞ ለሁሉም ሰቆቃ ማብቂያ እንዳለው ባረጋገጠበት የመስቀል ስራው የተገለጠ ነው፡፡

**የአንድ ሰው መከራ እና ሰቆቃ ከእግዚአብሔር የደረሰበት የሀጥያት ቅጣት መሆኑን እንዴት ማወቅ እንችላለን? እንደዛ እንደሆነ እርገጠኞች መሆን ካልቻልን፤ ያንን ሰው ልንቀርብ የሚገባን የተሻለ መንገድ ምን አይነት ነው? ወይም ስለራሳችን መከራና ችግር ሊኖረን የሚገባው አስተሳሰብ ምን አይነት ነው?**

# ተጨማሪ ጥናት

በዚህ ኳርተር መጀመሪያ እንደተመለከትነው በአንድ ታሪክ ውስጥ የምናገኛቸው ገፀባህሪያትን ድርጊት መነሾ እና ምክንያት ለመረዳት ራሳችንን በእነሱ ቦታ ማስቀመጥ ጠቃሚ ነው። እነሱ ልክ እንደኛ፤ ታሪክ በተለያየ ሁኔታ ውስጥ ሲቀጥል ከርቀት የሚመለከቱ አይደሉም።

ራሳችንንበኤልፋዝ በበልዳዶስ እና በሶፋር ቦታ አስቀምጠን ብናየው የቱ ጋ እንደተሳሳቱ ለመለየት ያን ያህል አይቸግረንም። ያን አይነት ውሳኔ ለመስጠት እነሱ ብቁ አልነበሩም።

"የሰው ልጅ ለባህሪው ታላቅ ጥፋቶች ሲከሰቱ የገነነ ወንጀል እና የጠለቀ ሀጥያት ውጤት እንደሆኑ ያስባል፡፡ ይህ እግዚአብሔር የበቀል ፍርድ የሚያወርድበት ዘመን አይደለም። መልካም እና ክፉ ተቀላቅለው ስለሚገኙ ጥፋት የሚመጣውም በሁለቱም ላይ ነው። አንዳንድ ግዜ ሰዎች የእግዚአብሔርን ከለላ አልፈው ይሔዱና ሰይጣን ሀይሉን ያቀምሳቸዋል የዛን ግዜ ግን እግዚአብሔር ጣልቃ መግባት አይችልም። ኢዮብ መራራ ስቃይ ደርሶበት ነበር፤ ጓደኞቹ ደግሞ የርሱ ስቃይ ከሀጥያት የተነሳ እንደደረሰበት እንዲያምን በመፈለጋቸው ኩነኔ እንዲሰማው አደረጉ። የኢዮብን ሁኔታ ከአንድ ከባድ ሐጥያተኛ ፍርድ ጋር አመሳሰሉት፤ እንደዛ በማድረጋቸው ግን እግዚአብሔር ገሰፃቸው። ኤለን ጂ ዋይት (SDA Bible Commentary, vol 3, # 140)

ለስቃይ እና መከራ መንስኤዎች ማብራሪያ ስንሰጥ ተጠንቀቀን ሊሆን ይገባል፡ በርግጥ አንዳንድ ግዜ ማብራሪያ መስጠት ቀላል ሊሆን ይችላል፡ አንድ ሰው ሲጋራ ስላጨሰ የሳንባ ካንሰር ያዘው። ከዚያም በላይ ቀላል ሊሆን ይችላል፡፡

**ነገር ግን እድሜ ልካቸውን ሲጋራ እያጨሱ የሳንባ ካንሰር የማይያዙትስ? እግዚአብሔር አንዱን እየቀጣ ሌላውን እየተወ ነው ማለት ነው?**

**በስተመጨረሻም፤ ልክ እንደ ኤልፋዝ፣ በልዳዶስ እና ሶፋር መከራ እና ስቃይ ለምን እንደሚመጣ አናውቅም። በአንድ ጎኑ ደግሞ ለምን እንደሚመጣ ብናውቅም ባናውቅም ፋይዳ የለውም። ፋይዳ ያለው የሚያጋጥመንን መከራ እና ስቃይ በተመለከተ የምንወስዳቸው አፀፋዊ ድርጊቶች ናቸው። እዚህ ጋ ነው እነዚህ ሶስቱ ሰዎች ሙሉ በሙሉ የሚሳሳቱት።**

## የመወያያ ጥያቄዎች:

1. ምንም እንኳን አሁን ሁኔታዎች ሌላ ቢሆኑም የእግዚአብሔር የበቀል ፍርድ እርሱ በመጨረሻ ቀን ፍርድ እንደሚያመጣ እንድናምን እንዴት ሊያግዘን ይችላል?

2. ሶስቱ የኢዮብ መካሪዎች (ጓደኞች) እርሱ በመከራው የደረሰበትን ሁሉ አልተረዱም ነበር። በተወሰነ መልኩ፤ ይህ የእኛም ባህሪ አይደል? ሰዎች ለምን መከራ እንደሚደርስባቸው ሙሉ በሙሉ አናውቅም። ታድያ ይህ እውነታ በሀዘን እና ሰቆቃ ላይለሚገኙ ሰዎች ርህራሔ እንድናሳይ እንዴት ሊረዳን ይችላል?